የኢትዮጵያ የፖለቲካ እስረኞች አንድነት ኮሚቴ (ኢፖእአኮ)
SOLIDARITY COMMITTEE FOR ETHIOPIAN
POLITICAL PRISONERS (SOCEPP)

መስከረም 26/2002

## የፖለቲካ እስረኞች መለቀቅ ቅድመ ሁኔታ መሆኑ ሲያንስ ነው

**የኢትዮጵያ የፖለቲካ እስረኞች አንድነት ኮሚቴ (ኢፖእአኮ) በፖለቲካ ድርጅቶች የፖለቲካ ውሳኔ ውስጥ ጣልቃ ገብቶ የሚተቸው ባይኖረውም ሰብዓዊ መብትን በተመለከተ ግን ድጋፍ ተቃውሞ ውን ማሰማት ግዴታው ነውና በቅርቡ የዳኛ ብርቱካን ሚዲቅሳ ድርጅት መሪ ከሆኑት አንዱ በሰጠው የራዲዮ መግለጫ ዳኛዋ ከእስር ብትፈታም ባትፈታም መፈታቷን ለምርጫ ተሳትፎ ቅድመ ሁኔታ አናደርግውም ባለው ላይ ኢፖእአኮ ልዩነቱን በግልፅ ማስፈር ይፈልጋል፡፡ ግለሰቡ ይህን ያለው ያውም ዳኛ ብርቱካን በቅርቡ ትፈታለች የሚለውን የአቶ መለስ አገዛዝ የውስጥ ውስጥ ፕሮፓጋንዳ በመፃረር የወያኔ አገዛዝ በስልጣን እሰካለ የምትፈታ አትሆንም ብሎ ደምድሞ ነው፡፡**

**ዳኛ ብርቱካን ሚዲቅሳ ከህገ ወጥ እስር ሳትፈታ በምርጫ አንሳተፍም ብሎ አቅዋም መውሰድ ተገቢ ብቻ ሳይሆን መወሰድ ያለበት አማራጭ አልባ ፍትሀዊ አቅዋም ነው፡፡ በመሰረቱ አንድ የታሰረ ግለሰብ ብቻ ሳይሆን በፖለቲካ ተቃውሞ የተነሳ የታሰሩት ብዙ ሺዎች ( ባለፈው ምርጫ የተያዙትን ሁሉ ጨምሮ) ሳይፈቱ በመጪው ምርጫ ዳግም ለመሳትፍ መወሰንና ለአፋኙ አገዛዝ መሳሪያ መሆን ተገቢ አይሆንም፡፡ የሰብዓዊ መብት መከበር ጥያቄ መሰረታዊ የዴሞክራ ሲ ጥያቄ ነው፡፡ ሰብዓዊ መብት በተረገጠበት፤ መብትን የጠየቁ ዘብጥያ በወረዱበት፤ የሕዝብ ድምፅ መሰረቁን የተቃወሙ መፈጀት ብቻ ሳይሆን በሺዎች በየማጎሪያው ተጥለው እስካሁን በሚሰቃዩበት ሁኔታና አሁንም ዜጎች እየታፈሱ በመታሰር ላይ እያሉ በምርጫ አለምንም ቅድመ ሁኔታ እንሳተፋለን ብሎ መነሳተና ለአገዛዙም ማሳወቁ- ምናልባትም የሚሰቃዩ ዜጎችን መርሳት ይሆናልና ሊታሰብበትና ሊቀየር የሚገባው አቅዋም ነው፡፡ ዳኘ ብርቱካንም፤ አበራሽ በርታም፤ የዴዴሳ፤ዝዋይ ብር ሸለቆና ሸዋ ሮቢት ወዘተ የፖለቲካ እስረኞች ሁሉ ይፈቱ የሚል ቅድመ ሁኔታ ማቅረብ ይገባል/ ይጠበቃል፡፡ ለመብት ሲታገሉ የታሰሩትን ረስቶ ለመብት እንታገላለን ማለት ዘበት ነው፡፡**

SOCEPP, POSTFACH 51213, BERLIN 13372,GERMANY
SOCEPP, 30 RIGA COVE, WINNIPEG,MB R2P 2Z7,CANADA
E MAIL: SOCEPP @AOL.COM
WEB SITE: WWW.SOCEPP.DE